**የበልግ የድንበር ሂደት ፡- የድኅረ ማጽደቅ ማሳወቂያ ደብዳቤ፣ በዌክፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክፍሎች 9-11 ቤተሰቦች**

ዲሴምበር 10፣ 2021

ውድ የዌክፊልድ ቤተሰቦች፡-

የትምህርት ቤቱ ቦርድ በዲሴምበር 2 ቀን 2021 ባካሄደው ሰብሰባ ከኦገስት 2022 ጀምሮ ተፈጻሚነት የሚኖረውን የበልግ 2021 የድንበር ማሻሻያ በማጽደቅ ድምጽ ሰጥቷል፡፡

የዕቅድ ዩኒቶች 46110፣ 46120፣ 46111፣ 48160፣ 48180፣ 48290፣ 46140፣ 48150፣ 48280፣ 48281 ለ2022-23 የትምህርት ዘመን ከዌክፊልድ ወደ ዋሽንግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ ይህ ለውጥ ለሁሉም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል (በ2021-22 በ8ኛ ክፍል)፣ እና ሁሉም ከላይ በተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች ነዋሪ በሆኑ አዲስ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በዌክፊልድ ከ9-11ኛ ክፍል ተማሪ የሆኑ ወይም በከጁን 17 ቀን 2021 በፊት በዌክፊልድ የሚመዘገቡ ተማሪዎች 12ኛ ክፍል እስኪጨርሱ ጊዜ ድረስ በዌክፊልድ ሊቀጥሉ ወይም ከ2022-23 የትምህርት ዘመን አዲስ በተመደቡበት በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ በሚገኝ ትምህርት ቤት (ዋሽንግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ሊማሩ ይችላሉ፡፡ በዌክፊልድ ለመቀጠል ለሚፈልጉ ተማሪዎች መደረግ የሚገባው ተጨማሪ ነገር የለም፡፡ **ከላይ በተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ የሚገኙ እና በአሁኑ ጊዜ ከ9ኛ -11ኛ ክፍል የሚገኙ ልጆቻቸው በ2022-23 የትምህርት ዘመን ትምህርት ቤት ቀይረው በዋሽንግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ እንዲማሩ የሚፈልጉ ቤተሰቦች እስከ ጃንዋሪ 27 ቀን 2022 ከዚህ የሚከተሉትን መፈጸም አለባቸው፡-**

- ልጅዎ በ2022-23 የትምህርት ዘመን በዋሽንግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማር/ትማር እንደሆነ ለማሳወቅ እባክዎን በዌክፊልድ የካውንስሊንግ ዳይሬክተር የአስተዳደር ረዳት ከሆኑት ሬይና ቤሪዮስ ጋር ይነጋገሩ፡፡
- ሚስስ ቤሪዮስ በ reyna.berrios@apsva.us ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-6702 ይገኛሉ፡፡

**ወንድምና እህቶች፣ እና የትራንስፖርት መረጃ**

- **ወንድምና እህቶች ፡-** በዌክፊልድ የ9ኛ -11ኛ ክፍል ተማሪዎች ወንድሞች/ እህቶች የሆኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ከላይ ከተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች መካከል በአንዱ ነዋሪ ከሆኑ በ2022-23 የትምህርት ዘመን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ከታላላቅ ከወንድሞቻቸው ወይም እህቶቻቸው ጋር በዌክፊልድ አብረው መማር እንዲችሉ ሊዘዋወሩ ይችላሉ፡፡
- **ትራንስፖርት ፡-** የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከላይ በሚገኙት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ ያሉ ነገር ግን በእግር ከሚደረስበት ዞን ውጪ ነዋሪ ለሆኑ ተማሪዎች በዌክፊልድ ቢቀጥሉም ሆነ በዋሽንግተን-ሊበርቲ ትምህርት ቤት ለመማር ቢመርጡ (በቅርቡ የተመደበ የአካባቢ ትምህርት ቤት) ትራንስፖርት ያቀርባል፡፡ በእነዚህ የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ከ9ኛ-11ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በዌክፊልድ ከቀጠሉ በመላው አገሪቱ በሚሰራው ሀብ ስቶፕስ አማካኝነት የትራንስፖርት አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ ተመራጩ ጥያቄዎን የማቅረብ ዘዴ በengage@apsva.us ኢሜል ማድረግ ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-2481 የዕቅድ እና ግምገማ ክፍልን ማነጋገር ነው፡፡ የበልግ 2021 የድንበር ሂደትን በተመለከተ እባክዎን ከዚህ የሚከተለውን ሊንክ ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/engage/fall-2021-boundary-process፡፡

አመሰግናለሁ፣

ሊሳ ስቴንግል
የዕቅድ እና ግምገማ ዳይሬክተር
አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች